# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## *የሴቶች መብት ያለገደብ ይከበር!*

የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም. (ማርች 8. 2013) በመላው አለም ለሴቶች መብት መከበር ተከራካሪ በሆኑ ድርጅቶች ግምባር ቀደምትነት በሰላም ወዳድ ኃይሎችና በሲቪል፥ መንግሥታዊ ባልሆኑና በተለያየ ደረጃ በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በመታጀብ በሴቶች ጥያቄ ላይ ያተኮሩ መግለጫዎችን በማውጣትና የተለያዩ ዝግጅቶችን ለሕዝብ በማሳየት ቀኑን እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ ዘንድሮም ይዘክሩታል።

ይህ የሴቶች ቀን አንዳንዴም የእናቶች ቀን በሚል ስያሜ የሚታወቀው አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በብዙ ሀገራት እንዲከበር በሕገ መንግሥታቸው ቢካተትም በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲያዊ ሥርአት በመሰረቱበት ሀገራት እንኳ ሴት ነክ የሆኑ መብቶች እንደ ቀላልና የተለመደ ተደርገው ቢታዩም ለዚህ ቀን መከበር ሲሉ በርካታ ሴቶች እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደው ከፍተኛ መስዋዕት የከፈሉበት መሆኑን የሚያስታውሱ ግን ጥቂቶች መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህ ከሁለት አመት በፊት መቶኛ አመቱ የተከበረው የሴቶች ቀን ከፍተኛ ቦታውንና ተገቢ ክብሩን በሁሉም ዜጎች ሕሊና ሰርፆ እንዲገባ ይህ የዛሬው የሴቶች ቀን መከበር ከሚያበረክታቸው አስተዋፅዖ መካከል አንዱ እንደሆነ በስፋት የሚገለፅ ነው።

ኢሕአፓ ጤናማ ለሆነ የዜጎች ግንኙነት፥ በሰላማዊ ኑሮ ላይ ለሚመሰረት ለማህበራዊና ለኤኮኖሚ እድገት የሴቶች ጥያቄ በተገቢው ሁናቴ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል የሚል የጸና እምነት እንዳለው በተደጋጋሚ የገለፀውና ለተግባራዊነቱም አበክሮ የሰራበትና ወደፊትም የሚሰራበት ነው። በዚህም ምክንያት ነው ሴቶች የነፃነት መብታቸውን ባልተጎናፀፉበት ጤናማ የፖለቲካ ሥርአት ሰፍኗል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም በማለት ሳያለሰልስ የሚገልፀው። ከማህበረሰባችን ውስጥ ከግማሽ ቁጥር በላይ የሆኑት ሴቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መብታቸው በርግጠኝነት ሳይከበርላቸው፥ እኩልነታቸው በቃል ሳይሆን በገቢር ሳይረጋገጥላቸው በሀገራቸው በራሳቸው መብት ዙሪያ ሙሉ ተሳትፎና የችግሮቻቸው የመፍትሄ አካል ሊሆኑ አይቻላቸውም። የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል በመሆናቸውም ሕብረተሰቡ ራሱ ባጠቃላይ ነፃነቱን ሳይጎናፀፍ ሴቶችም የነፃነት ካባ ሊላበሱ እንደማይችሉ ግልፅ ነው። ግማሽ ነፃነት የለምና።

ለዚህም ነው የወያኔ አገዛዝ የሕገ አገዛዛቸውን አንቀፅ 35 ደጋግመው ቢገልፁም በመፃፉ ብቻ የፖለቲካ ጠቀሜታ ያስገኝልናል በማለት ከሚያምኑት ጥቂቶች በስተቀር ብዙሃኑ የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳን ክብደት የሌለው መሆኑን ሴቶች በእለት ተለት መብት አልባ ኑሮ ለመኖር መገደዳቸው የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው። አሁንም ድረስ ወንድ


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ልጅ ወልዶ ማሳደግ አጋዥና አጋር ማግኘት በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ሴት ልጅ መመኘት በወንዶቹ ባጠቃላይ የወንድ ማናህሎኝነት በሰፈነበት ሁኔታ ደስተኛ አለመሆን በተለይም በገጠሩ አካባቢ የተስፋፋ ነው። ለግርድና የተቀጠሩ ወጣት ሴቶች ሳይወዱ በግዴታ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚደፈሩ በርካታ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ባለባቸው የኑሮ ችግር የተነሳም አማራጭ በማጣትና ኃፍረትን በመፍራት፣ ተበድለውም በበዳይነት ላለመፈረጅ ሲሉ ዝምታን የሚመርጡ ቤቱ ይቁጠረው ማለቱ የሚቀል ነው። ለድብደባና ለአካል ጉዳት ለመሳሰሉ የኃይል ጥቃት የሚዳረጉት ሴቶች መሪር ሀዘናቸው ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለቅርብ ዘመዶቻቸው የመንፈስ ስቃይን እያተረፈና ማህበራዊ ኑሮን እያናጋ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

ሴቶች ለበርካታ ዘመናት ከሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መነፈግ ጋር በፆታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው ያለው ድርብ በደልና ጭቆና ተገልፆ የማያልቅ ሰቆቃ ነው። ሴቶች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የሚያድጉት የወንድ የበላይነት ሰፍኖ ባለበት ሕብረተሰብና የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ በመሆኑ ለተለያዩ የአካላትና የስነልቦናዊ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። ለጠለፋ፣ ለአስገድዶ መድፈርና ድብደባ ለመሳሰሉት የወንጀል ተግባራት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሁኔታው ተጋጥሞላቸው ዘመናዊ ትምህርት የቀመሱ ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ሴቶች እንኳ ሳይቀሩ ቤተሰብ ሲመሰርቱ ለትዳራቸው መጎልበት የራሳቸው ገቢ የሌላቸው በመሆናቸው የበላይና የበታች ብሎም የጥገኝነት ስሜት የሚያሳድርባቸው ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ለሚኖር አለመግባባትም የራሱ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ በገሃድ የሚታይ ነው። የወሊድ ክትትል ለማድረግም ቢሆን እየተስፋፋ ባለው ድህነትና የገንዘብ አቅም በማጣት፣ በአቅራቢያ በስፋት የሕክምና ተቋማት ባለመኖር ምክንያት ለእናቶችና ለሕፃናት ሕይወት መቀጠፍ በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው።

ሕጋዊና ተቋማዊ አሰራሮች ሴቶችን አሁንም ለጥቃት ከመጋለጥ አላዳናቸውም። በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በስራ ቦታና በሌሎችም ሕዝባዊ ቦታዎች በሴቶች ላይ በወንዶች የሚፈፀሙ ጾታዊና አካላዊ ጉዳቶች በርካታ ናቸው። የሚያሳዝነው ደግሞ ወንድን ሳይሆን ሴትን በውበቷና በፆታዋ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው አሳፋሪ ምክንያታዊ ገለፃዎች ናቸው። የወጣት ሴቶች መንገድ አዳሪነትና ለወሲብ ባርነት፣ በአደንዛዥ ዕፀዋት ሱስ መውደቅ፣ ለወንዶች ብዝበዛና ዋልጌነት መዳረግ፣ ለድብደባና ጨካኝ ቅጣት ጭምር መጋለጥ፣ ቀኑን እየጠበቀ በሚመጣው ረሃብና ችግር በብዛት ሰለባ እየሆኑ ያሉ በርካታዎቹ ሴቶችና ሕፃናት  ናቸው። ድህነትን ለመሸሽ በወያኔ አገዛዝ ዋና አቀናባሪነት ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ለዘመናዊ ባርነት ተዳርገው ለስቃይና ለሞት የተጋለጡ ሴቶች ዜጎቻችን በርካታ ናቸው። ታዲያ የሴቶች ሁናቴ በሀገራችን ባጭሩ ይህን ሲመስል የወያኔ አገዛዝ የሴቶችን እኩልነት በተግባር የሚያረጋግጥ በሕገ አገዛዙ አስፍሬያለሁ እያለ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም ከ 22 አመታት በኋላም ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየው የመብት መከበርን ሳይሆን በበለጠ መገፈፍን ከድህነት መላቀቅን ሳይሆን ይበልጥ በመብት አልባ ምክንያት መደህየትን ነው።

ዛሬ የካቲት 29 ቀን ሲከበርና ሲዘከር ለሴቶች መብት መከበር ሲታገሉ መስዋዕት የከፈሉትን በርካታ እህቶቻችንና እናቶቻችንን በሕሊናችን እያስታወስን፣ ለእስር የተዳረጉትን ደግሞ ፅናቱን እንዲሰጣቸው ብቻ ሳይሆን ከእስር ተፈትተው ከዘመዶቻቸው በሰላም እንዲገናኙ የይፈቱ ጥሪ በማቅረብ ነው። ከ1993 ዓ.ም. ጀምሮ መዳረሻዋ ያልታወቀው እውቋ የኢሕአፓ ታጋይ አበራሽ በርታና እንዲሁም የቀይ ሽብር ሰለባ አፀደ ወይን፣ ገነት ክፈለው፣ ምር አት አሰገድ፣ አበበት ካሳ፣ አላማዝ ጠፉ፣ ግርሚትአለም ደገፉና ሌልቹም የዚሁ አገዛዝ ሰለባ የሆኑት ምንጊዜም ከሕሊናችን የማይጠፉ በልባችን ኃውልት የሰራልናቸው ናቸው። በሀገራችን በወያኔ አገዛዝ ስለ ሴቶች እኩልነት ያልተፃፈ፣ ያልተወራ፣ ያልተለፈለፈ ፕሮፓጋንዳ የለም። በፕሮፓጋናዳ ብዛት ግን የሚሻሻል ሁኔታ ወይንም የሚገኝ ለውጥ ጨርሶ የለም። ሕብረተሰቡም ሆነ ሴቶች የነፃነት መብታቸውን ስላልተጎናፀፉ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ገና አልተከበረላቸውም። እጅግ በጣም የሚቆጠሩ የአገዛዙ አባላት የሆኑ ሴቶች ምንም አይነት በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ሚና በሌላቸው ምክር ቤቶቻቸው ስለተቀመጡ ብዙሃኑ ሴቶች ከመድረኩ ተገለውና ተጨቁነው መገኘታቸውን አይሸፍነውም። ከከፋ ድህነት ለመገላገል የሚያስችላቸው የፖለቲካ ሥርአትና ምህዳር ገና አላገኙም።

በመሆኑም በዛሬው ቀን አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ስናከብርና ስንዘክር የት ነበርን? የት ደርሰናል? ምንስ ይቀረናል? ለሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ሁኔታውን ገምግሞ መፍትሄ በመስጠት አሁንም መብታቸው በገቢር እንዲረጋገጥ በቀጣይነት ሴቶችን መቀስቀስ፣ እየቀሰቀሱም ማደራጀት፣ እየተደራጁም መታገል የግድ እንደሚል እንገነዘባለን። ስለሆነም የሴቶች ጉዳይ በቀጡ ይመለከተኛል የሚል ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ በዝግጅታቸው ተካፋይ በመሆን በአላቸውን በዓላችንን እንዲደምቅና ትግላቸው ትግላችን ስምሪት እንዲያገኝ ኢሕአፓ በዚህ አጋጣሚ የከበረ የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

ኢሕአፓ የሴቶች መብት ያለገደብ ይከበር ሲል ለተራ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን ከልቡ የሚያምንበት ለመሆኑ በአባልነት ተሰልፈው ለሴቶች መብት ሲታገሉ የተሰዉ፣ የቆሰሉ፣ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሁሉና አሁንም በአባልነት ግዳጃቸውን እየተወጡ የሚገኙ የሴት አባላቱ ድርጊቶቻቸው ምስክር ናቸው። እነዚህን ኢሕአፓ ከልብ ያደንቃል። የክብር ምስጋናም ይለግሣቸዋል። በመንፈስም በአካልም የቀይ እቅፍ አበባ ያበረክትላቸዋል። ያለ ሴቶች ደማቅ ተሳትፍ ትግላችን አይሰምርምና የዛሬው በአላቸው የትግልና የድል ጉዳና እንዲከፍት ልባዊ ምኞቱን ሲገልፅ በኩራት ነው።

የሴቶች መበት የማይከበርበት ሥርአት አምባገነናዊ ነው!!
ድል ለሴቶች ትግል!